የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN
COMMUNICATIONS AUTHORITY

# የቴሌኮሙኒኬሽን ህጋዊ ታሪፍ መመሪያ

# ቁጥር 797/2013

2013 ዓ.ም

# የቴሌኮምኒኬሽን ህጋዊ ታሪፍ መመሪያ

ባለስልጣኑ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ታሪፍ ህጋዊነትን ለማምገም፣ ታሪፍ ለመጨል ወይም ታሪፎችን ለማለስ ተግባር ላይ የሚያወላቸው ህጎች እና የአሰራር ስርሃቶች ላይ ግልጽነትን መፍጠር በማስፈለጉ፥

የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች ታሪፍ ሲቀይሩ ወይም አዲስ ታሪፍ ሲያስቀምጡ ባለሰልጣኑን የሚያወቁበት ስርሃቶች ላይ ግልጽነት መፍጠር በማስፈለጉ፥

የቴሌኮምኒኬሽን ኦፕሬተሮች ለሚሰጡት አገልግሎት ህጋዊ ያልሆኑ ታሪፎችን እንዳይጠይቁ ማከልከል አስፈላጊ በመሆኑ፤

ባለስልጣኑ በኮሚኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 አንቀጽ 6(2)፣ 6(6)፥ 45(5) እና 46(1) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የቴሌኮምኒኬሽን ህጋዊ ታሪፍ መመሪያ ቁጥር 797/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ፤

   1) **"ገባሪ መሠረተ ልማት"** ማለት አንቴናዎች፥ ሰዊቾችን፣ ሰርቨሮችን፣ የሚጃ ቋቶችን፣ የማከፋፈያ ወይም የሬዲዮ መዳረሻ ኖድ እና የማስተላለፊያ መሣሪያዎችን ጨምሮ በገባሪ የቴሌኮሚኒኬሽን ኔትዎርክ ንብርብር ላይ ያሉ ክፍሎች ወይም አካላት ናቸው፤
   2) **"ባለሥልጣን"** ማለት በኮሚኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለሥልጣን ነው፤
   3) **"ኮሎኬሽን"**ማለት አንድ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ለአገልግሎት አቅርቦት የሚጠቀምባቸውን የኔትዎርክ መሳሪያዎች ወይም ሥርዓቶች የሌላኛው የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የኔትዎርክ መሳሪያዎች ወይም ሥርዓቶች የተገጠሙበት ስፍራ ላይ በሁለቱ መካከል በሚደረሰው ስምምነት መሠረት ቴክኒካዊ አግባብነት ባለው ቦታ በአንድ ላይ ማስቀመጥ ነው።
   4) **"ቁጥጥር የሚደረግበት ታሪፍ"** ማለት በባለስልጣኑ አግባብነት ባለው ገበያ ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ አለው ተብሎ የተወሰነ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ለሚሰጠው አገልግሎት ወይም ጥቅል አገልግሎት የሚጥለው ታሪፍ ነው፥
   5) **"ቁጥጥር የሚደረግበት የችርቻሮ ታሪፍ"** ማለት አግባብነት ባለው የችርቻሮ ገበያ ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ አለው ተብሎ የተወሰነ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ለሚሰጠው የችርቻሮ አገልግሎት የሚጥለው ታሪፍ ነው፥

6) " **ቁጥጥር የሚደረግበት የጅምላ ታሪፍ**" ማለት አግባብነት ባለው የጅምላ ገበያ ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ አለው ተብሎ የተወሰነ የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር ለሚሰጠው የጅምላ አገልግሎት የሚጥለው ታሪፍ ነው፥

7) "**የታችኛው ክዋና**" ማለት የችርቻሮ አገልግሎት የሚሰጥ እና ተዋሪዳዊ በሆነ ሚልኩ የተደራጀ ኦፕሬተር የንግድ ስራ ሲሆን የችርቻሮ ንግድ አቅርቦቱን ሲያከናወን በህግ የተለየ እና ራሱን የቻለ ሌላ ተቋም ስራወን በሚሰራበት ሚልክ ነው።

8) "**የታችኛ የችርቻሮ ዋጋ**" ማለት የታችኛ ክዋኔ ወጪ ማለት ነው፡፡

9) "**መሠረተ ልማት ማጋራት**" ማለት በተዋዋዮቹ መካከል የሚደረገው ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የማሰረተ ልማት እና የኮሎኬሽን አቅራቢ ከማሰረተልማት እና ኮሎኬሽን ፈላጊ ጋር ቋሚ እና ገባሪ መሠረተ ልማቶችን የሚጋሩበት የተለያየ አሰራር ሲሆን የኔትወርክ ክፍሎችን፣ ሥርዓቶችን፣ መሣሪያዎችን፣ አገልግሎቶችን፣ ቅጥር ግቢዎችን ወይም የማጠቀም መብቶችን ጨምሮ ሌሎችንም ያካትታል።

10) "**የህዳግ ጥበት**" አግባብነት ባለው የችርቻሮ ገበያ ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር የችርቻሮ ንግድ ወስጥ ላሉ ሌሎች ተወዳዳሪ የቴሌኮም ኦፕሬተሮች የጅምላ ሽያጭ በማከናወን የችርቻሮ ዋጋን እና የጅምላን ዋጋ ሲወስን እና ባስቀማጠው የጅምላ እና የችርቻሮ ዋጋ መካከል ያለው የዋጋ ልዩነት በችርቻሮ ንግድ ወስጥ ያለ የተሻለ አፈጻጸም እና ወጤታማ የሆነ ተወዳዳሪ አገልግሎት እየሰጠ ወድድር ወስጥ መቆየት የማያስችለው ሁኔታ ሲከሰት የሚፈጠር ነው።

11) "**ማስወቂያ ሰጪ**" ማለት ቁጥጥር የሚደረግበትን ታሪፍን ለመቀየር ወይም አዲስ ታሪፍ ለመተግበር ፍቃድ ለማግኘት ለባለሥልጣኑ የፅሁፍ ማስወቂያ የሚያቀርብ የቴሌኮምኒኬሽን ኦፕሬተር ነው።

12) **ቋሚ መሠረተ ልማት**" ማለት የገባሪ ቴሌኮሚኬሽን ኔትወርክ መሠረተ ልማት ንብርብር አካል ያልሆነ መሠረተልማት ሲሆን የሥሬ ቦታዎችን፣ ሕንፃዎችን፣ ማጠለያዎችን፣ ማማዎችን፣ ረገሾም ቋሚዎችን፣ ምሶሶዎችን፣ ማስተኛ ጉድጓዶችን፣ ጠብብ ቦዮችን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እና የአየር ማቀዝቀዣን ጨምሮና ሌሎችንም የሚያካትት ማሰረተ ልማት ነው።

13) "**ከገበያ ማስወጫ ዋጋ**" ማለት ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር ተፎካካሪ ወይም ተፎካካሪ ሊሆን የሚችልን የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር ሆን ብሎ ለመጣል ወይም መጣል የሚችልበትን ሁኔታ በማሰብ ለአጭር ግዜ ኪሳራ ወስጥ መግባት ወይም የሚያገኘወን ትርፍን መተው ነው።

14) "**የችርቻሮ አገልግሎት**" ማለት ለሚጨረሻ ተጠቃሚው ወይም ለደንበኛ የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን ለቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ አገልግሎትን አያካትትም፡፡

15) "**ጉልህ የገበያ ድርሻ**" **ማለት** ማለት ለኮሚኬሽን አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ ማልገያዎችን ወይም በገበያ ወስጥ ያለወን ድርሻ አቅም በማጠቀም በኮሚኬሽን አገልግሎት ዋጋ ወይም አቅርቦት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የማሳረፍ ችሎታ ነው፤

16) "**ጉልህ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር**" ማለት አግባብነት ባለው ገበያ ወስጥ ጉልዕ የገበያ ድርሻ እንዳለው የተወሰነ የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር ሲሆን ለብቻው ወይም ከሌሎች አከላት ጋር በጥምረት በማሆን የሚፈጥረው ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም የገበያ የበላይነትን የሚሰጠው ሲሆን የኢኮኖሚ ጥንካሬው በሚታይ ሚልኩ ከተወዳዳሪዎች፣ ደንበኞች እንዲሁም የሚጨረሻ ተጠቃሚዎች ነጻ በሆነ ሚልኩ እንዲንቀሳቀስ የሚያስችል አቅም ይሰጠዋል፡፡

17) **"በተዋረደ የተቀናጀ ኦፕሬተር"** ማለት የችርቻሮ እና የጅምላ አገልግሎቶችን የሚቀርብ የቴሌኮምኒኬሽን ኦፕሬተር ነው።

18) **"የጅምላ አገልግሎት"** ማለት ለሌላ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ የቴሌኮሚኒኬሽን፣ የኮሎኬሽን ወይም የመሠረተ ልማት መጋራት አገልግሎት ነው፡፡

19) **"የስራ ቀናት"** ማለት ስራ የሚከራባቸው ቀናት ብቻ ሲሆኑ ቅዳሜ እሁድ እና ማናቸውንም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ የበዓላት ቀን የተባለ ነው፡፡

**3. ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላሞዎች፡

1) በአዋጁ አንቀጽ 45 እና 46 መሰረት ባለሰልጣኑ የማንኛውንም የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ታሪፍ ህጋዊነት ለማምግሞ፣ ታሪፍ ለመወሰን እና ታሪፎችን ለመከለስ ተግባር ላይ የሚውላቸው ህጎች እና የአሰራር ሰርሃቶች ላይ ግልጽነትን መፍጠር፥
2) የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ታሪፍ መቀየር ወይም አዲስ ታሪፍ ማስቀመጥ ሲፈልግ ለክተላቸው የማቡ ህጎች ላይ ግልጽነት መፍጠር፥
3) የቴሌኮምኒኬሽን ኦፕሬተሮች ለአገልግሎቶቻቸው ህጋዊ ያልሆኑ ታሪፎችን እንዳይጠይቁ መከልከል፤

ነው።

**4. የተፈጻሚነት ወሰን**

1) ይህ መመሪያ ቴሌኮምኒኬሽን፣ ኮሎኬሽን፣ እና መሠረተ ልማት መጋራት አገልግሎቶች ታሪፍ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።
2) ይህ መመሪያ በኢትዮጲያ ፌደራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ወስጥ በሚገኙ ሁሉም የቴሌኮምኒኬሽን ኦፕሬተሮች ላይ ተግባራዊ ይሆናል። ይሁን እንጂ በግልጽ ሲመለከት የተወሰኑ ደንጋጌዎች አግባብ ባለው ገበያ ወስጥ ጉልህ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ሁለት

## የባለሥልጣኑ ሚና

**5. የባለሥልጣኑ ሚና**

1) ባለሥልጣኑ፡

ሀ) የሁሉም የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች ታሪፍ ህጋዊነትን ያረጋግጣል እንዲሁም ግልጽነታቸው እንዲጨምር ይሰራል፤

ለ) ህጋዊ ታሪፎችን ለመዛን እና ለመወሰን የሚያስችሉ እና ከፍተኛ መተማመን የሚፈጥሩ ስታንዳርዶችን እና የአሰራር ስርአቶችን ይዘረጋል፤ እና፣

ሐ) የሁሉንም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ታሪፍ ሕጋዊነት ለሚያጋግጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ ግምገማ ያደርጋል ፤ እንዳስፈላጊነቱም ለአገልግሎት የተቀመጡ ታሪፎችን ሕጋዊነታቸውን ለሚያጋግጥ ቁጥጥር ያደርጋል።

2) ባለሥልጣኑ፡

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ 45 (4) መሠረት ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር ያወጣው ማንኛውም ታሪፍ በባለስልጣኑ እስከጸደቅ ድረስ ተፈጻሚነቱ እንዲዘገይ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ለ) በራሱ ወይም በአንድ ወገን ጠያቂነት ጥሪቃ በመግባት የአንድ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ታሪፍ ህጋዊነትን ይወስናል፤

## ክፍል ሦስት

## የሕጋዊ ታሪፎች አጠቃላይ መርሆች

### 6. የሕጋዊ ታሪፎች አጠቃላይ መርሆች

1) በአዋጁ አንቀፅ 45(1) መሠረት ሁሉም የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች የሚጠይቁት ክፍያ በተጠቃሚዎች ወይም በተጠቃሚ መደቦች መካከል አግባብ ያልሆነ አድልዎ የማይፈጥር ተገቢና ምክንያታዊ መሆን አለበት።
2) አገልግሎት ገዢ ስለ አንድ ጊዜ ክፍያ ፣ ስለ ተደጋጋሚ ክፍያዎች እና ቅናሾች ሙሉ መረጃ ሊኖረው ስለሚገባ ታሪፎች በይፋ ወይም በግልፅ መንገድ ሊገለፁ ይገባል።
3) ታሪፎች አንድ ምርት ወይም አገልግሎት ለማቅረብ መሰረታዊ ወጪዎችን ከግምት ወስጥ ማስገባት አለባቸው።
4) በተመሣሣይ ደምቦች እና ሁኔታዎች የሚሰጡ ተመሳሳይ የችርቻሮ አገልግሎቶች ታሪፎች በገዢዎች ወይም በገዢ መደቦች መካከል ተመሳሳይ መሆን አለባቸው።
5) ለራሱ እና ለሌላ ኦፕሬተር ተመሳሳይ የጅምላ አገልግሎት የሚሰጥ በተወራድ የተቀናጀ ኦፕሬተር በተመሳሳይ ደምቦች እና ሁኔታዎች አገልግሎቱን ማስጠት አለበት።

## ክፍል አራት

## ቁጥጥር የሚደረግባቸው ታሪፎችን ፋይል ስለማድረግ እና ስለ ማፅደቅ

### 7. ቁጥጥር የሚደረግባቸው የችርቻሮ እና የጅምላ አገልግሎቶች ታሪፎችን ፋይል ስለማድረግ እና ማፅደቅ

1) የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ቁጥጥር የሚደረግበት አዲስ ታሪፍ ለማስተዋወቅ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበትን ታሪፍ ለመለወጥ ሲፈልግ ይህኑ ለባለስልጣኑ የማሳወቅ እና እንዲያጸድቅለት ማጠየቅ አለበት። እንዲህ

ዓይነቱ ማስወቂያ በሚወጣው ታሪፍ ላይ ማስረታዊ ለውጥ በሚፈጥሩ በዋጋ ሊገለጹ በሚችሉ ወሎች ላይም ተፈጻሚ ይሆናል።

2) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የጽሑፍ ማስታወቂያ በተቀበለ በአሥራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ውስጥ፡

ሀ) ታሪፉን ማፅደቅ፤

ለ) ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት ማስወቂያ ካቀረበው አካል ተጨማሪ መረጃን መጠየቅ፤ ወይም

ሐ) የቀረበውን ታሪፍ ወደቅ ማድረግ እና ወደቅ የተደረገበትን ምክንያት በጽሁፍ ማሳለጽ፤

አለበት።

3) ማስወቂያ ያቀረበ አካል ያቀረበው ታሪፍ በባለሥልጣኑ ካልፀደቀ በቀር ተግባራዊ ሊደረግ አይችልም።

4) ባለሥልጣኑ የቀረበውን ታሪፍ ለተጨማሪ አስር (10) የሥራ ቀናት ለማግምገም በማስብ ሚራዘም ይችላል።

5) ባለሥልጣኑ በአስራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ጊዜ ወይም ተፈጻሚ የሚሆን ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ወስጥ ማስወቂያ ላቀረበው አካል ሜልስ ካልሰጠ ታሪፉ እንደፀደቀ ይቆጠራል።

6) አሳዋቂው አካል ታሪፉ ከፀደቀ ከሰባት (7) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ የተፈቀደውን ታሪፍ በድረ-ገፁ ላይ ማዙም አለበት።

7) ባለሥልጣኑ የቀረበውን ታሪፍ የሚፀድቅ ከሆነ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት:

ሀ) ለአሳዋቂው አካል የቀረበው ታሪፍ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ያሳውቃል፤ ወይም

ለ) በአዋጁ አንቀጽ 46 ፣ በዚህ መመሪያ እና በባለሥልጣኑ በጸደቁ ሜችወም መመሪያዎች መሰረት ቁጥጥር የሚደረግባቸው ታሪፎችን ህጋዊነታቸውን ለሚፈጋገጥ ታሪፍ የማግምገም ሂደት ይጀምራል፡፡

8) በዚህ መመሪያ ወስጥ የተመለከቱ የትኛችም ድንጋጌዎች ቢኖሩም፤ ቁጥጥር የሚደረግበት ታሪፍ በባለሰልጣኑ ሜጽደቁ በአዋጁ አንቀጽ 48 ላይ ያሉትን የፀረ-ወድድር አሠራሮችን ድንጋጌዎች ወይም ባለሥልጣኑ ያፀደቀውን ማንኛውንም መመሪያ ተግባራዊ ከሜድረግ ነፃ አያደርግም።

## ክፍል አምስት

## የዋጋ አወጣጥ መርሆች

### 8. ቁጥጥር የሚደረግባቸው የጅምላ አገልግሎቶች ታሪፍ የዋጋ አወጣጥ መርሆች

1) ቁጥጥር የሚደረግባቸው የጅምላ ታሪፎች:-

ሀ) ዋጋ-ተኮር፤ እና

ለ) አድሎአዊ ያልሆኑ፤ መሆን አለባቸው።

2) ቁጥጥር የሚደረግበት የጅምላ ታሪፍ ዋጋ-ተኮር መሆኑን ለማግምገም ባለሥልጣኑ ፣

ሀ) ወደፊት ሊኖር የሚችል የወጪ ጭማሪ የዋጋ ዘዴ፤ ወይም

ለ) አግባብ ያለው የጅምላ ታሪፎች ዓለም አቀፍ ልምድን፤ ይጠቀማል።

3) ባለስልጣኑ ወደፊት ሊኖር የሚችል የወጪ ጭማሪ የዋጋ ዘዴን በማጠቀም ቁጥጥር የሚደረግበት የጅምላ ታሪፍ ሲገማም የሚከተሉትን መርሆዎች ተግባራዊ ያደረጋል፡

ሀ) ወደፊት ሊኖሩ የሚችሉ ወጭዎች አንድ ወጤታማ የሆነ ኦፕሬተር የተወሰነ አገልግሎትን ለማስጠት የሚያወጣቸው ወጪዎች ናቸው።

ለ) የወጪ ማሰረት የሚከተሉት የወጪ ዘዴዎችን በማጠቀም ይቀመጣል፡

i) ማሉ ወጪዎች;

ii) በረጅም ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ ወጪ ወይም

iii) የተደመረ በረጅም ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ ወጪ ይህም (የጋራ እና መደበኛ ወጪዎችን ያካትታል)

4) በአለም አቀፍ ተሞክሮዎች ላይ ማሰረት በሚደረግ ቁጥጥር የሚደረግበት የጅምላ ታሪፍ ሲገማም ፤ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ዳታዎች ጥቅም ላይ ያወላል፡-

ሀ) የተማከተወን አገልግሎት ታሪፍ ለመወሰን የፊት ምልከታ የዋጋ ጭማሪ ዘዴን የተጠቀሙ ሃገራት ; እና

ለ) ከኢትዮጵያ ጋር ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ተቀራራቢነት ያላቸው ሃገራት።

5) ባለሥልጣኑ በንዐስ አንቀፅ (3) እና (4) ላይ የተማከቱትን አሚራጮች ተግባራዊ በሚደረግ ቁጥጥር የሚደረግበትን የጅምላ ታሪፍ ለማገምገም የሚያስችል አስተማማኝ መረጃዎችን ማግኘት ካልቻለ እና:-

ሀ) የጅምላ አገልግሎት አቅራቢ ስምምነት ወስጥ ካለው ከሌላኛው ወገን ተመጣጣኝ የሆነ የጅምላ አገልግሎት የሚቀበል ከሆነ፤ ወይም

ለ) ባለሥልጣኑ የሚቻቻል ዘዴ ምክንያታዊ እንደሆነ ከወሰነ፤

የሚቻቻል ዘዴ ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፡-

6) አገልግሎቶቹን ለማቅረብ በሚወጡ ወጪዎች ወይም በሚጠበቁ ወጪዎች ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የጅምላ አገልግሎት አቅራቢ በተመሳሳይ ወሎች እና ሁኔታዎች ስር ለሚቀርቡ ተመሳሳይ አገልግሎቶች የተለያዩ ኦፕሬተሮችን የተለያየ ክፍያ የሚያስከፍል ከሆነ፣ ቁጥጥር የሚደረግበት ታሪፍ አግባብ ባልሆነ መልኩ አድሎዎ እንደፈጠረ ይቆጠራል።

7) የጅምላ አገልግሎትን የሚያቀርብ በተዋረድ የተቀናጀ ኦፐሬተር በስሩ ላለ የታችኛው ክዋኔ አገልግሎቱን የሚያቀርብበት ዋጋ በተመሳሳይ አገልግሎት ላይ ለተሰማሩ ሌላ ኦፐሬተሮች ከሚያቀርብበት

ዋጋ ያነሰ እንደሆነ፤ ቁጥጥር የሚደረግበት ታሪፍ አግባብ ባልሆነ ሜኩ አደሰዎ እንደፈጠረ ይቆጠራል።

8) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 ላይ የተመለከተውን የጅምላ አገልግሎትን ለራስ ከማቅረብ ጋር የተገናኙ ወጪዎችን ለማከላት፤ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተመለከተውን የፊት ምልከታ ወጪ ጭማሪ ዘዴን ተግባራዊ ያደረጋል።

**9. ቁጥጥር የሚደረግበት የችርቻሮ አገልግሎቶች የዋጋ ማውጫ መርሆች**

1) ባለሥልጣኑ ፋይል የተደረገ ቁጥጥር የሚደረግበት የችርቻሮ ታሪፍ ሕጋዊነት ለሚጋገጥ ግምገማ ሲያከናውን ታሪፉ ከገበያ የሚየስወጣ መጣራን ወይም የህዳግ መጥበብ መጣራን ማለፍ ይጠበቅበታል፣ በተጨማሪ አግባብ ባልሆነ መልኩ አድሎአዊ መሆን የለበትም፡፡

2) ባለስልጣኑ የችርቻሮ ታሪፍ ከገቢያ አስወጪ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ሲገመግም የሚከተሉትን ነጥቦች ግንዛቤ ወስጥ መከተት አለበት፦

ሀ) ለሚመለከተው አገልግሎት ወይም ጥቅል አገልግሎት የተቀመጠው ታሪፍ ከወጣበት ወጪ ያነሰ ነው ወይስ አይደለም፡ ታሪፉ ከወጣው ወጪ ጋር እኩል ወይም ከፍ ያለ ከሆነ፤ ከገበያ ማስወጫ ዋጋ መጣራን አልፎል።

ለ) የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፐሬተሩ ወቅታዊ የበጀት አመቱ ወጪ ወይም የሚገኝ ከሆነ ለቁጥጥር ስራ የወጣ ወጪ እንደ ሚጃ ምንጭ በመወሰድ የአንድን አገልግሎት ወጪዎችን ያሰላል።።እነዚህ ወጪዎች የተወሰዱት ካለፈው ዓመት ከሆኑ ለአገልግሎቱ የወጣው ወጪ ሲሰላ ምክንያታዊ የሆነ ማስተካከያ ይደረግበታል።

ሐ) የወጪዎን መሠረት ለመወሰን ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን የወጪ ተግባራዊ ያደርጋል፦

i) ሙሉ ወጪ

ii) በረዥም ግዜ እየጨመረ የሚሄድ ወጪ፤ ወይም

iii) ተደማሪ እየጨመረ የሚሄድ ወጪ ይህ የጋራ እና መደበኛ ወጪዎችን ያካትታል፡፡

3) ባለስልጣኑ ቁጥጥር የሚደረግበት የችርቻሮ ንግድ የህዳግ ጥበት መጣራን ያልፋል ወይስ አያልፍም የሚለውን ነጥብ በሚገመገምበት ወቅት፤ የሚከተሉትን ነጥቦች ግንዛቤ ወስጥ ያስገባል፦

ሀ) የሕዳግ ጥበት መኖሩን ይመዝናል፤

ለ) በችርቻሮ ታሪፍ እና የችርቻሮ አገልግሎት ለማቅረብ በሚያስፈልገው ወጪ መካከል ያለው ልዩነት አወንታዊ መሆኑን ይገመግማል። በችርቻሮ ታሪፍ እና የችርቻሮ አገልግሎቱን ለማስጠት በሚወጣው ወጪ መካከል ያለው ልዩነት አወንታዊ ከሆኑ፣ ታሪፉ የህዳግ ጥበት መጣራን እንዳለፈ ይቆጠራል።

ሐ) የችርቻሮ አገልግሎት ወጪዎችን ለማስላት በጅምላ ንግድ ወስጥ የተገዙ አስፈላጊ ግባቶች ወጪ እና የታችኛው የችርቻሮ ወጪ ግንዛቤ ወስጥ በመከተት የሚሰላ ይሆናል።

መ) በተዋረድ የተቀናጀ ኦፕሬተር የታችኛው የችርቻሮ ወጪ እንደ ከታች ያለ ወጪቃማ የሆነ ተወዳዳሪ ኦፕሬተር የችርቻሮ ወጪ አድርጎ በመውሰድ የችርቻሮ አገልግሎት አቅርቦት ወጪ ያሰላል፡፡

ሠ) የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሩን ወቅታዊ የበጀት ዓመት ወጪ ወይም የሚገኝ ከሆነ የቁጥጥር ወጪዎችን እንደ ምንጭ በማጠቀም በተዋረድ የተቀናጀን ኦፕሬተር የታችኛው የችርቻሮ ወጪ ይሰላል። እነዚህ ወጪዎች የተወሰዱት ካለፈው ዓመት ከሆኑ ለአገልግሎቱ የወጣው ወጪ ሲሰላ ምክንያታዊ የሆነ ማስተካከያ ይደረግበታል።

ረ) ) የችርቻሮ ንግድ የወጪ መሠረት ለመወሰን ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን የወጪ

i. ሙሉ ወጪ

ii. በረጅም ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ ወጪ፤ ወይም

iii. ተደማሪ በረጅም ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ ወጪ ይህ የጋራ እና ሚዛበኛ ወጪዎችን ያካትታል፡፡

## 10. ያልተገባ የዋጋ መድሎ

አገልግሎቶቹን ለማቅረብ በሚወጡ ወጪዎች ወይም በሚጠበቁ ወጪዎች ልዩነት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር አግባብነት ባለው ገበያ ውስጥ በተመሳሳይ ወሎች እና ሁኔታዎች ለሚቀርቡ ተመሳሳይ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎችን ወይም የተጠቃሚ መደብን የተለያየ ክፍያ ማስከፈል አይችልም።

# ክፍል ስድስት

# የታሪፍ ክለሳዎች

## 11. የታሪፍ ክለሳዎች

1) ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 46 መሰረት ፈቃድ ያለውን ማንኛውም የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ታሪፍ የመቆጣጠር ወይም የማጣጣም ስልጣን አለው።

2) ባለስልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ወይም ፍላጎት ባለው ማንኛውም አካል ጠያቂነት የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ታሪፍ ህጋዊ መሆኑን ለሚረጋገጥ ጉዳዩን የመጫከት ሂደት ሊጀምር ይችላል።

3) ባለስልጣኑ ታሪፍ የማከለስ ሂደት ለመጀመር ከወሰነ ክለሳው የጅምላ ንግድ ወይም የችርቻሮ ንግድን ማሰረት በማድረግ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 እና 9 ላይ የተመለከተ የዋጋ መርህን መከተል አለበት።

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ጉዳዩን የመጫከት ሂደት ለመጀምር ከወሰነ ፤ በአዋጁ ከአንቀጽ 35 እስከ 38 እንዲሁም ከዚህ በታች የተመለከቱ የአሰራር ስርሃቶች ማሰረት በማድረግ ይሆናል፡-

ሀ) ባለስልጣኑ የታሪፍ ግምገማን በማከናወን እና ታሪፍን በመወሰን ህጋዊነትን ለሚረጋገጥ የቁጥጥር ሂደት መጀመሩን ፍላጎት ላላቸው አካላት የሕዝብ ማስወቂያ በማውጣት ይገልጻል፤

ለ) ማስወቂያው የመወያያ ነጥቦችን መያዝ ያለበት ሲሆን በዚህም የታሪፍ ክለሳው ለምን እንደሚከናወን እና ባለስልጣኑ ታሪፉ ህጋዊነትን እንዲላበስ ሊከተል ያሰባው አካሄድ ምን እንደሆነ ማካተት አለበት።

ሐ) ማስታወቂያው ፍላጎት ያላቸው አካላት አስተያየታቸውን ፋይል ከሚድረጊያ ማስፈርት ጋር የሚያስገቡበት እና ለህዝባዊ ምክክር የሚቀርብበትን የጊዜን ርዝሜ ማካተት አለበት።

መ ) ባለሥልጣኑ ፍላጎት ላላቸው ወገኖች ምላሽ ለማስጠትና አስተያየቶችን ለማቅረብ ከአሥራ አምስት (15) ያላነሱ የሥራ ቀናት ማስጠት አለበት።

ሠ) ባለሥልጣኑ ከሚሳከታቸው አካላት አስተያየቶችን ከተቀበለ በኋላ ለተቀበለው አስተያየቶች ምላሹን ከአሥራ አምስት (15) ባልበለጠ የሥራ ቀናት ወስጥ ማስጠት አለበት በዚህም-

i) ለእያንዳንዱ አስተያየት ሜልስ በማስጠት የሜጨሻ ወሳኔ ያሳልፋል; ወይም

ii) ለእያንዳንዱ አስተያየት ሜልስ ይሰጣል፤ አስፈላጊም ሲሆን የሜጨሻ ወሳኔ ከማስጠቱ በፊት ሀለተኛ የወይይት ነጥብ በማቅረብ ፍላጎት ያላቸው አካላት ከአሥራ አምስት (15) ባላነሱ የሥራ ቀናት ወስጥ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ያደርጋል።

ረ) ባለሥልጣኑ በራሱ ምርጫ የሜጨሻ ወሳኔ ከማስጠቱ በፊት ፍላጎት ካላቸው አካላት ከሁለት (2) ዙሮች በላይ አስተያየቶችን ሊቀበል ይችላል።

ሰ) ባለስልጣኑ ወሳኔወን በጽሑፍ ማስጠት አለበት። ለወሳኔው ማስረት የሆኑት ማስረታዊ ምክንያቶችም በወሳኔው ወስጥ ማካተት አለባቸው።

## **ክፍል ሰባት**

## **የሂሳብ ደብተር ማሳየት**

**12. የሂሳብ ደብተር ማሳየት**

1) ባለሥልጣኑ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት አቅራቢወን ለጅምላ ሽያጭ አገልግሎት አግባብነት ባለው ገበያ ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው ከወሰነ እና አገልግሎት ሰጪው የችርቻሮ አገልግሎት የሚስጥ በተዋረድ የተቀናጀ ኦፕሬተር ከሆነ ከአገልግሎቱ ጋር የተያያዙ ገቢ እና ወጪዎችን ማሳየት እንዲቻል በሕግ ራሱን ችሎ እንደሚሰራ ኩባኔያ የጅምላ ሽያጭ የተለየ የሂሳብ ማዝገብ ሜያዝ አለበት።

2) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የሂሳብ አያያዝ እንዴት ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት የሚያሳይ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## **ክፍል ስምንት**

## **ታሪፎችን ለህዘብ ማሳወቅ**

**13. በባለሥልጣኑ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ታሪፎች ህትመት**

1) ባለስልጣኑ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ አግባብነት ባላቸው ገበያዎች ምርት ላይ ጉልህ የገበያ ድርሻ አለው ብሎ የወሰነው የቴሌኮም አፕሬተር በድረገጹ ላይ ታሪፋን ማውጣት አለበት።

2) ባለስልጣኑ የጸደቁ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ታሪፎችን የተመለከቱ በቂ እና ወቅታዊ የሆኑ ኢንፎርሜሽኖች በደረገጹ ላይ ያወጣል ወይም እንዲወጣ ያደርጋል።

## ክፍል ዘጠኝ

## ሕግ ማስፈጸም እና ሕግ ማክበር

**14. ህግን ማክበር**

ባለሥልጣኑ ቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተሮች የአዋጁን እና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ማክበራቸውን ይቆጣጠራል።

**15. ሕግ ማስፈጸም**

1) ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ፣ አዋጁ እና ባለስልጣኑ ያጸደቃቸውን መመሪያዎች መሰረት በሚድረግ የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተሩ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ጥሷል ብሎ ከወሰነ፤ በአዋጅ አንቀጽ 52 መሠረት እርምጃ የሚወስድ ሲሆን እርምጃው የገንዘብ ቅጣት ወይም ሁኔታዎችን ወደነበረበት መመለስ ሊሆን ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለስልጣኑ የሚያስቀምጣቸው መፍትሄዎች እና ቅጣቶች በአዋጁ አንቀጽ 52(6) መሠረት ፈቃድ ስለማሰረዝ፣ እገዳ እና ሌሎች የአስተዳደር እርምጃዎች እና ቅጣቶች እንዲሁም የቅጣት ማጠኖች ለመወሰን በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡

## ክፍል አስር

## ልዩ ልዩ አቅርቦቶች

**16. ሚስጥራዊነት**

በዚህ መመሪያ መሠረት በቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተሮች የሚሰጥ መረጃ ሚስጥራዊ ከሆኑ፤ ባለስልጣኑ የመረጃወን ሚስጥራዊነት ለማጠበቅ ምክንያታዊ የሆኑ እርምጃዎችን መወሰድ አለበት፡፡

**17. የይግባኝ መብት**

ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጠው ማንኛውም ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ በአዋጁ አንቀጾች 38 እና 39 መሠረት ሚልሶ ሊታይ እና ይግባኝ ሊጠየቅበት ይችላል፡፡

**18. ማሻሻያ**

ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ግዜ ፈቃድ ለተሰጣቸው አገልግሎት ሰጪዎች አስቀድሞ በማሳወቅ እና በአዋጁ መሠረት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት ይህንን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

**19. መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ--------2013 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ በ _______ ቀን___________ 2013 ዓ.ም**

**ኢንጂነር ባልቻ ሬባ**

የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር